# የኛና የናንተ

አዲስ ፖለቲካ ፤ የነሱና የኛ
የበረከት መለስ ፤ ያዲሱ ጉልተኛ
የትላንት ባንዳዎች ፤ የዛሬ አርበኛ
ልበ ሙቅ አስመሳይ ፤ አፍ ብቻ ፤ ጉረኛ
የየ ድርጅቱ ፤ ቀላዋጭ ሱሰኛ
እራስን ማሞገስ ፤ እንዳይቀር ወገኛ
ለቃቅሞ አዳሪ ፤ አንጃና ቅጥረኛ
ያምናው ፤ ቡከን ሁሉ ፤ ደነፋ ግምኛ ።

እዩኝ እዩኝ ማለት ፤ በየቦታው መሮጥ
የኛና የናንተ ፤ እያሉ መቅበጥበጥ
ከሻቢያ ከተገንጥይ ፤ ደጃፍ መቀላወጥ
እግር ተዘርግቶ ፤ ጥድፊያ ለመቀመጥ
አንድም ፤ ለመሞት ነው ፤ አሊያም መፈጥፈጥ
ልክን አለማወቅ ፤ ካቅም በላይ ማበጥ ።

ገዳይ በየለቱ ፤ እየጎለበተ
የኛ የናንተ እያለ ፤ አስመሳይ ታበተ
እኔም እየሞትኩኝ ፤ እሱም እየሞተ
ድል ይገኝ ይመስል ፤ ስለተዶለተ
ጎራ እየተበጀ ፤ በኛና የናንተ
ባስመሳይ ታጋዮች ፤ ትግሉ ተጎተተ
ወንድሙን ሊገጥም ፤ ሰራዊት ከተተ
ጠላት አስቀምጦ ፤ ወዳጅ ላይ ዘመተ ።

አፍራሹን ፤ በታኙን ፤ እየቀላቀሉ
ጎጠኛና ካድሬ ፤ ሰግስጎ መሃሉ
መመሪያ ከጠላት ፤ እየተቀበሉ
ለስልጣን አቋራጭ ፤ ተመርጦ ቀላሉ
ላንድ ፤ አላማ እንዳይቆም ፤ እየነጣጠሉ
የኛና የነሱ ፤ ብለው ደለደሉ
በምኞት አይሆንም  ፤ እነሱ ስላሉ
ትግል መች ይሰምራል ፤ ያምራል እንደ ቃሉ
እንደ ጀግና ታግለው ፤ ሞተው ካልገደሉ ።

ታዛቢው